# ዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ

## ናውሩዝ 177

ለዓለም ባሃኢዎች

እጅግ የምትፈቀሩ ወዳጆች፣

1 ወቅታዊ ኩነቶች በዚህ ጊዜ ለእናንተ እንድንጽፍላችሁ እና እስከ ሪዝቫን እንዳንጠብቅ አስገድደውናል። ሁላችሁም በሚገባ እንደምትገነዘቡት፣ በቅርብ ሳምንታትና ወራት፣ ስጋት ላይ የወደቀ ዓለም፣ ህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለው ውጤት እስካሁን በምንም ዓይነት እርግጠኝነት መገመት ያልተቻለ፣ በብዙ ሀገሮች ህዝቦችን እየጎዳ ያለ፣ በፍጥነት እየተባባሰ የሚለወጥ የጤና ቀውስ በማስተናገድ ላይ ነው። ልክ እንደኛ፣ እናንተም፣ የሰው ዘር ደህንነት፣ በተለይ እነዚያ እጅግ የተጋለጡት፣ በከፍተኛ ሁኔታ እንዳሳሰባችሁ እርግጠኞች ነን። ከዓለም አቀፍ መድረክ እስከ ታች ወርዶ፣ የህብረተሰቡ የተባበረ ጥንካሬ፣ በተግባር ላይ በሚገለጸው አንድነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ በርካታ ጊዜ የበለጠ ግልጽ ሆኗል፤ እናም በዚህ ረገድ የሁሉንም ጤናና ደህንነት ለመከላከል እገዛችሁን እየተደረጉ ላሉ አስፈላጊ ጥረቶች እየሰጣችሁ እንደሆነ እናውቃለን።

2 ወቅታዊ ሁኔታው በብዙ ቦታዎች በአምላክ እምነት አስተዳደር ላይ ተጽዕኖ ማሳረፉ አይቀሬ ነው፣ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የሚመለከተው ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ መወሰድ ስላለበት ተገቢ እርምጃ ምክር ይሰጣል። ይህ በአንዳንድ ሃገሮች ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ በሌላ መንገድ እንዲመረጥ ዝግጅቶች በማድረግ፣ ብሔራዊ ስብሰባዎችን መሰረዝን ያጠቃልላል። በአንዳንድ ቦታዎች፣ የአካባቢ መንፈሳዊ ጉባዔዎችን ለመምረጥ ተመሳሳይ ዝግጅቶች ሊደረጉ ይገባ ይሆናል። ሆኖም ግን፣ ይህንን እንኳን ለማድረግ የማይቻል ከሆነ፣ በዚህ ዓመት የአካባቢ ወይም የብሔራዊ ጉባዔዎች ያላቸውን አባላት ለሚቀጥለው የአስተዳደር ዓመት ማስቀጠላቸው የተፈቀደ ነው። ማንኛውም ይህን ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ እያሰላሰለ ያለ ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ የአማካሪዎችን ምክር ገና ከጅምሩ መጠየቁ ተገቢ ነው።

3 በሌላ ቀውስ ጊዜ፣ አብዱል ባሃ እነዚህን የምክር ቃላት ለግሷል፡- “እነዚህን በመሰሉ ቀናት፣ የፈተናና መከራ ኃይለኛ ነፋሶች ዓለምን በከበቧት ጊዜ፣ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ምድርን ሲያሸብሯት፣ እንደ አምላክ ፍቃድ፣ የፍራቻና ድንጋጤ ጭጋግ ሙሉ በሙሉ ተጠራርገው በሚወገዱበትና ተስፋ ሰጪው ብርሃን ከተከሰተው አድማስ በብሩህነት በሚያበራበት መልኩ፣ በበሩ ፊቶችና ብሩህ ግምባሮች፣ ከአይበገሬነትና ጽናት አድማስ በላይ መውጣት አለባችሁ።” ዓለም እምነት የሚያጎናጽፈውን የተስፋና የመንፈስ ጥንካሬን እያደገ በሚሄድ መልኩ በሚያስፈልጓት ሁኔታ ላይ ትገኛለች። የምትፈቀሩ ወዳጆች፣ በእርግጥ ለረዥም ጊዜ በቡድን ውስጥ ባሉ ነፍሶች ውስጥ በትክክል ለዚህ ጊዜ የሚያስፈልጉ ባህሪያትን ኮትኩቶ የማሳደግ ሥራ ላይ ተጠምዳችሁ ቆይታችኋል፡- አንድነትና የአብሮነት ስሜት፣ ዕውቀትና ግንዛቤ፣ የጋራ አምልኮና አንድ ዓይነት የጥረት መንፈስ። በእርግጥ፣ እንቅስቃሴዎቻቸውን ለመገደብ ከቻሉ ሁኔታዎች ጋር በተጋፈጡበት ጊዜ እንኳን፣ እነዚህን ባህሪያትን ለማጠናከር የተደረጉ ጥረቶች እንዴት ማህበረሰቡን በተለይ ችግርን ተቋቁሞ ማለፍ የሚችል እንዳደረጉት መመልከታችን ነክቶናል። ከአዲስ ሁኔታዎች ጋር መላመድ ቢኖርባቸውም፣ አማኞች የወዳጅነት ትስስሩን ለማጠናከር፣ እንዲሁም በእነርሱ መካከልና ከሚያውቋቸው ጋር መንፈሳዊ ንቃተ ህሊናንና የስክነትን፣ ልበ ሙሉነትንና በአምላክ የመተማመን ባህሪያት ለማራመድ፣ ፈጠራ የተመሉ መንገዶችን ተጠቅመዋል። የዚህ ውጤት የሆኑ ከፍ ያሉ ጭውውቶች፣ በርቀትም ይሁን በአካል፣ ለብዙዎች የመጽናናትና የመነቃቃት ምንጭ ሆነዋል። በእናንተ በኩል እንዲህ ያሉ ጥረቶች፣ በርካታ ነፍሳት ግራ በተጋቡበትና ባዘኑበት በዚህ ሠዓት ውድ የሆነ ግልጋሎትን ያበረክታሉ። ምንም እንኳን አሁን ነገሮች ቢከብዱም፣ ምንም እንኳን አንዳንድ የማህበረሰቡ ክፍሎች የመቋቋም አቅማቸው ገደብ ጋር ቢደርሱም፣ የሰው ዘር ይህንን መከራ በስተመጨረሻው ያልፈዋል፣ እናም በሌላኛው በኩል፣ ስለመሠረታዊ አንድነቱና እርስ በእርስ ትስስሩ ከፍ ያለ እይታና ጥልቅ የሆነ ጥቅሙን መረዳትን ይዞ ብቅ ይላል።

4 አሁን፣ የባሃኢ ዓለም ባለፈው ዓመት የተቀዳጃቸውን ስኬቶች በማንኛውም ዓይነት ዝርዝር፣ ወይም ሁኔታዎች በፈቀዱ ቦታ ሁሉ በቅንነት የሚሰራው፣ የማህበረሰብ ግንባታ እንቅስቃሴውን በዓለም ዙሪያ በማበራከትና የእድገት መርሃግብሩን በማጠናከር ረገድ የተደረጉ እጅግ ከመጠን በላይ የሆኑ ግስጋሴዎችን፣ የምንገልጽበት ጊዜው አይደለም።

በያሁኑ እቅድ ውስጥ አራት ዓመት ሲቆጠር፣ የማይታከቱ የእምነቱ ደጋፊዎች የባሃኦላህን እምነት በታሪኩ ውስጥ ከነበረበት ሁሉ እጅግ ጠንካራ የሆነ ደረጃ አድርሰውታል፣ ማለቱ ይበቃል። የሰራችኋቸው እና እየሰራችኋቸው ያሉት ሁሉም ነገሮች ሉላዊ የባሃኢ ማህበረሰቡን በመለኮታዊ እቅዱ ሂደታዊ የመገለጽ ሂደት ለሚቀጥለው ደረጃ ማዘጋጀት ነው።

5 ለአሁኑ ሀሳቦቻችንና ጸሎቶቻችን፣ በሁሉም የአምላክ ወዳጆችና በሁሉም አብራችኋቸው በሚኖሩት፣ ጤናና ደህንነት ላይ አተኩረዋል። እንዲሁም፣ እጅግ ኃይል የተመላው መተማመንን፣ ብርታትንና ጽናትን እንዲለግሳችሁ በቅንነት እንጸልያለን። አዕምሮዎቻችሁ ሁሌም ላላችሁባቸው ማህበረሰቦች ፍላጎቶች፣ ስለምትኖሩባቸው ሕብረተሰቦች ሁኔታዎች፣ እንዲሁም ለሁሉም ወንድሞችና እህቶች ለሆናችኋቸው ስለመላው የሰው ዘር ያሰላስሉ። በጸጥታ ጊዜያችሁ፣ ከጸሎት በስተቀር ሌላ ምንም ማድረግ የሚቻል በማይመስልበት ጊዜ፣ ያኔ፣ መከራው እንዲያከትም የናንተን ተማጽኖ ከእኛ ጸሎት ጋር እንድታክሉት እንጋብዛችኋለን። ሙሉ ህልውናቸው ለሌሎች ደህንነት ከራስ የተላቀቀ መሠጠት ወደሆነው፣ ወደ እነዚህ የአብዱል ባሃ ቃላቶች እንዞራለን፡-

> አቤቱ አንተ ሰጪው ሆይ! እነዚህ ክቡር ወዳጆች የአንተን መልካም ፍቃድ እንዲቀዳጁ እርዳቸው፣ እንዲሁም ለእንግዶችና ለወዳጆች በተመሳሳይ መልካም ተመኚዎች አድርጋቸው። ለዘላለም ወደሚኖረው ዓለም አምጣቸው፤ የመንግስተ ሰማይዊ ጸጋ ድርሻ ስጣቸው፤ በቅንነት የአምላክ የሆኑ እውነተኛ ባሃኢዎች አድርጋቸው፤ ከውጫዊ መምሰል ጠብቃቸው፤ እናም በእውነቱ ላይ በጽኑ አቁማቸው። ከዝቅተኛው ህይወት አድማስ በላይ የሚያበሩ የመንግስቱ ምልክቶችና መገለጫዎች አድርጋቸው። የሰው ዘር ህዘን አብራጅና አጽናኝ እንዲሁም የዓለም ሰላም አገልጋዮች አድርጋቸው።

ዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ